በሰነዓ ውስጥ የተመዘገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ስደተኞች አሁን ሰነዶቻቸውን በመደበኛነት በሰነዓ በሚገኘው **የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ** ማደስ ይችላሉ። ወቅታዊ የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነድ መያዝ እንደ ጥገኝነት ጠያቂ ወይም ስደተኛ የመን ውስጥ ለርስዎ ጥበቃ አስፈላጊ ነው እንዲሁም በUNHCR እና በብሄራዊ ባለስልጣናት **የሚሰጡትን አገልግሎቶች** ያመቻቻል።

ከኦክቶበር **15 2023** በኋላ፣ **UNHCR** የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸውን ሰነዶች ለያዙ ግለሰቦች አገልግሎት አይሰጥም።

ከዚህ ቀን በኋላ ወደ **UNHCR** ወይም ወደ አጋሮቹ የሚመጡ ግለሰቦች እርዳታ ከመደረጉ በፊት በመጀመሪያ ሰነዶቻቸውን በስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ማደስ አለባቸው።

የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መመዝገቢያ ማዕከል፣
የኢሚግሬሽን፣ የፓስፖርት እና የዜግነት ባለስልጣን ግቢ፣ ሳቢን ወረዳ፣ አል-ካውላን ጎዳና፣ ሰነዓ ከተማ፣ የመን

ሁሉም እርዳታ እና አገልግሎቶች **ከክፍያ ነፃ** ናቸው።

የሰነ ምግባር ጉድለትን ሪፖርት ለማድረግ፣ እባክዎ የሚከተሉትን ያነጋግሩ፡
UNHCR ጥበቃ የቀጥታ የስልክ መስመር: **+967 71 222 5038**
UNHCR ጥበቃ ኢሜይል: yemsaprt@unhcr.org
ዋና ኢንስፔክተር ቢሮ: inspector@unhcr.org

UNHCR
The UN Refugee Agency

በሰነዓ - የመን የተመዘገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ስደተኞች ሰነዶች እና አገልግሎቶች ማግኘት

UNHCR
The UN Refugee Agency

ሰነዴን በቀጥታ ከ UNHCR ማደስ እመርጣለሁ። ይህን እንዴት ማድረግ እችላለሁ?

እንደ አለመታደል ሆኖ UNHCR በየመን ጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነድ አያወጣም ወይም አያድስም። UNHCR ሁሉንም ጥገኝነት ጠያቂዎች እና ስደተኞች ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ቀርበው ሰነዶቻቸውን እንዲያድሱ በጥብቅ ያበረታታል። ጊዜው ያለፈበት የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ምስክር ወረቀት **ከአክቶበር 15 2023** በኋላ ከያዙ፣ አገልግሎቶች እና እርዳታ ማግኘት አይችሉም።

የአገልግሎቶች መቋረጥ በጤና አገልግሎት ተደራሽነት ላይ ተጽዕኖ ያመጣል?

ከ**አክቶበር 15 2023** በኋላ ጊዜው ያለፈባቸው ሰነዶች ላላቸው ግለሰቦች የሚሰጠው አገልግሎት መቋረጥ በUNHCR እና በአጋሮቹ ከሚሰጡ አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ ነው።

የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ሰነዶቼን ካደሰ፣ መልሶ የማቋቋም መብት አለኝ?

የእርስዎን እና የቤተሰብዎን ሰነዶች ማደስ እርስዎን የመልሶ ማቋቋም መብት አይሰጥዎትም። መልሶ ማቋቋም መብት አይደለም፣ የመልሶ ማቋቋሚያ ቦታዎች በጣም ጥቂት ስለሆኑ፣ የመልሶ ማቋቋሚያ እድል ሊገኝ የሚችለው በየአመቱ በጣም ትንሽ ለሆኑ ስደተኞች ብቻ ነው። እርስዎ እና ቤተሰብዎ በUNHCR እና በአጋሮቹ የሚሰጡትን አገልግሎቶች እና እርዳታ ማግኘት እንዲችሉ ሰነዶችዎን ማደስ ለእርስዎ አስፈላጊ ነው።

መታወቂያ ካርዴን ለማደስ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መሄድ አልችልም። UNHCR በመጓጓዣ ወጪዎች ሊረዳኝ ይችላል?

እንደ አለመታደል ሆኖ UNHCR የግለሰብ የመጓጓዣ ወጪዎችን ወይም ከሰነድ እድሳት ሂደት ጋር የተያያዙ ሌሎች ወጪዎችን ለመመለስ አቅም የለውም።

የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነዴን የማደስ ሂደት ምንድ ነው?

የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነድ ለማደስ፣ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ በአካል ቀርበህ ኦርጅናሉን (ጊዜ ያለፈበትን) የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነድ ይዘህ መገኘት አስፈላጊ ነው። ሁሉም የቤተሰብዎ አባላት በአካል ከእርስዎ ጋር መሄድ አለባቸው። ሁሉም የቤተሰብዎ አባላት ከሰነዶችዎ ጋር በአካል መገኘት አለባቸው።

ልጆች ካሉዎት፣ የልደት ወረቀቶቻቸውን እና/ወይም ሌላ የቤተሰብ አባል የሆኑ የማንነት ማረጋገጫ ሰነድ፣ ለምሳሌ ጊዜ ያለፈባቸው ፓስፖርቶች ይዘው መምጣት አለብዎት።

ከዛ በሃላ፣ ሁለት ቅጾች ይሰጥዎታል፡-

- **የማንነት ማረጋገጫ ቅጽ፡-** ማንነትዎን ለማረጋገጥ በአከባቢዎ ሽማግሌ እና በአቅራቢያዎ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ የሚሞላ፣
- **የሕክምና ምርመራ ቅጽ፡-** ይህ ቅጽ ይሰጠሃል። ከዛ በሃላ፣ የግዴታ የደም ምርመራ ለማድረግ ወደ ብሄራዊ ማዕከላዊ የህዝብ ጤና ላብራቶሪዎች ትላካለህ። ቅጹ በምርመራው ውጤት ተሞልቶ በብሔራዊ ማዕከላዊ የህዝብ ጤና ላብራቶሪዎች ማህተም ይታተማል። እባክዎን ለሰነድ እድሳት አስፈላጊ የሆኑ እና በብሔራዊ የማዕከላዊ የህዝብ ጤና ላብራቶሪዎች የሚደረጉ ማናቸውም የሕክምና ምርመራዎች ከክፍያ ነጻ መሆናቸውን ልብ ይበሉ።

እነዚህን ቅጾች ከሞሉ በኋላ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መውሰድ አለብዎት። በዚያን ጊዜ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ የሰነድ እድሳት ጊዜዎን ለማረጋገጥ የቀጠሮ ወረቀት ይሰጥዎታል።

ጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነዴን አጠፋሁ። ምትክ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?

ሰነድህ ከጠፋብህ፣ ከስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ምትክ ሰነድ መጠየቅ ትችላለህ። መተኪያ ሰነድ እንዲወጣ በመጀመሪያ የሚከተሉትን ማድረግ አለብዎት:

- መታወቂያዎን እንደጠፋዎት የሚያረጋግጥ ማስታወቂያ በአገር ውስጥ ጋዜጣ ላይ ማውጣት፣
- በመኖሪያዎ አቅራቢያ በሚገኘው ፖሊስ ጣቢያ በመሄድ መታወቂያዎ እንደጠፋብዎት ማሳወቅ፣ እንድሁም መታወቂያዎ እንደጠፋ ማመልከቱን የሚያረጋግጥ የፖሊስ ማሳወቂያ መጠየቅ።

እነዚህ ሁለት እርምጃዎች ከተጠናቀቁ በኋላ፣ ተዛማጅ ሰነዶችን (የማስታወቂያውን እና የፖሊስ ማሳወቂያውን ቅጂ) ይዘው ምትክ ሰነድ ለመጠየቅ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መቅረብ ይችላሉ። የጠፋብዎትን ሰነድ አላግባብ መጠቀምን ለመገደብ እባክዎን ለ UNHCR ማሳወቅዎን ያረጋግጡ።

ሰነዱን ለማደስ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መቅረብ አልችልም ምክንያቱም አካለ ጉዳተኛ ነኝ/የመንቀሳቀስ ችግር አለብኝ። የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነዴን እንዴት ማደስ እችላለሁ?

ከዕድሜ፣ ከአንቅስቃሴ ወይም ከሌላ የጤና እክል ጋር በተያያዘ ምክንያት ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ለመድረስ ተግባራዊ ተግዳሮቶች ላጋጠማቸው፣ ያሉበትን ሁኔታ ለማስረዳት UNHCR በአቤቱታ እና ግብረመልስ ዘዴ በኩል ማነጋገር አለባቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች UNHCR የቤት ጉብኝት እንድደረግ ከስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ጋር መገናኘት ይችላል፣ በሌላ ሁኔታዎች ደግሞ UNHCR ለመመዝገብ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መሄድ ያለበትን ግለሰብ በኢጋሮቹ እንዲረዳ ሊጠይቅ ይችላል።

የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ የሪፈራል ወረቀት ሰጥቶኝ ነበር። የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነድ ማግኘት እችላለሁ?

ለጥገኝነት ጠያቂዎች/ስደተኞች የተሰጡ ሪፈራል ወረቀቶችን የመተካት ሂደት ቀጥሏል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የሪፈራል ወረቀታቸውን በአዲስ የጥገኝነት ጠያቂ/ስደተኛ ሰነድ እንዲተካላቸው ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ እንዲቀርቡ ይበረታታሉ።

ከዚህ ቀደም ለመኖሪያ ፈቃድ አመልክቼ ነበር፣ ነገር ግን የመኖሪያ ፍቃዴን ለማደስ ክፍያ መክፈል አልችልም። ሆኖም የጥገኝነት ጠያቂ/የስደተኛ መታወቂያ ካርዴን ለማደስ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ በሄድኩበት ወቅት፣ የጥገኝነት ጠያቂ ሰነዴን ለማደስ ቅድመ ሁኔታ እነዚህን ክፍያዎች እንድከፍል ጠየቁኝ? ክፍያውን ለመክፈል አቅም የለኝም። ምን ማድረግ አለብኝ?

UNHCR የተጠራቀመ የመኖሪያ ክፍያ ላለባቸው ግለሰቦች ሁኔታ ከስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ጋር መወያየቱን እና መፍትሄ እንዲሰጠው መማከሩን ቀጥሏል። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ለጊዜው እነዚህን ጉዳዮች መፍታት አልቻልንም።

ሰነዶቼን አድሻለሁ፣ ነገር ግን በደረሰኝ ሰነድ ላይ ስህተት አለ። ይህ እንዲታረም/እንዲስተካከል መጠየቅ እችላለሁን?

አዎ፣ በወጣው ሰነድ ላይ ስህተት ወይም የፊደል ስህተት ካለ፣ ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ ተመልሰህ ይህ እንዲስተካከል መጠየቅ አለብህ። የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ እርማት እንድያደርግ፣ ትክክለኛ መረጃ የያዘ ኦፊሴላዊ ሰነድ ይዘው ወደ የስደተኞች ጉዳይ ቢሮ መምጣት አስፈላጊ ነው።